# <u>የዘር ማጥፋት ወንጀል!!</u>

ወያኔ ዛሬ በቤኒሻንጉል ትናንት በቤንች ማጅ ጉራፈርዳ ውረዳ አማራውን ለይቶ የማፈናቀልና አማራ የአማራ ከሚባለው ክልል ውጭ ሠርቶ የመብላትና የመኖር መብቱን መንፈጉና እንደ ውጭ ዜጋ በማየት በገር ውስጥ ከአንዱ ቦታ ወደ አንዱ ቦታ እንኳ እንዳይንቀሳቀስና ምርጫው ወደ ውጭ አገር የመፍለስ ብቻ እንዲሆን ማድረጉ ምን ያህል በከፋና አደገኛ ወቅት ላይ ያለን መሆናችን በግልጽ እያሳየን ነው።ሂትለር በጀርመን በይሁዳዎች ላይ ከፈፀመው ብምን ይለያል? በሽግግሩ ወቅት ጠቅላይ ሚንስትር በነበረው ታምራት ላይኔና በወቅቱ ፕረዘዳንት በነበረው መለስ ዜናዊ በተፈራ ዋልዋ አቀናባሪነት በተሰጠ ትእዛዝ በወተር፤አርባ ጉጉና በደኖ ኦህዴድና ኦነግን በየፊናው አስማርተው የኋላ ድጋፍ እየሰጡ ውድ ወገኖቻችን ህይወታቸው ሳታልፍ እንደ እንሰሳ ቆዳቸው መገፈፉ፤ሳይሞቱ በገደል ሲጣሉና ሕጻን ሽማግሌ ሴት ወንድ ሳይለይ በጅምላ ማለቃቸውን ሳንረሳው ዛሬ ደግሞ የባሰ የጠብ አጫሪነትና የምን ታደርጉኛላችሁ እብሪት የተሞላበትን ተግባሩን ጀምሯል።ከዚህ ቀደምም ይህ እኩይ መንፈሳዊና ብሔራዊ ሞራል የጎደለው፤ሃሳበ ድውይና ኩድኩድ ቡድን ለ17 ዓመታት ያህል በበጌምድርና በወሎ የፈጸመውን ዘግናኝ ዘር የማጥፋት ተግባሩን ረስታችሁታልና አስታውሱት ብቻ ሳይሆን የትም አትደርሱም የሚል ንቀት ሲሆን ወያኔ የተነሳበትን የመገንጠልና የኢትዮጵያን አንድነት የመበታተን ዓላማ ስኬታማ ለማድረግ በኢትዮጵያውያን መካከል ለረጅም ዘመናት ደርጅቶና ጸንቶ የኖረውን አጠቃላይ የአንድነትና የአብሮነቱን አሴት በመናድ ለ21 ዓመታት ተግባራዊ እያደረገ የመጣ መሆኑን ከድርጊቱ የአፈጻጸም  ባህሪና ደፍርሰው ባደሩ ቁጥር በአደባባይ የሚዘላብዱትን ትኩረት ሰጥተን ስንመለከት ለአጭርና ለረጅም ጊዜ የታቀዱ የድርጅቱ መርሆዎች መሆናቸውን እንገነዘባለን።ይህ አናሳ ቡድን ድሮ በበርሃ ዛሬ በቤተመንግሥት ሆኖ በየጊዜው የሚወስዳቸውን ርምጃዎች ደምረን ስንመለከትና ከበርሃ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በድርጅቱ ውስጥና ከድርጅቱ ውጭ የሚገኙ የአማራ ተወላጆች ላይ ያደረሰው እልቂት ከዚህ ወዲያ ማብቂያውና የመጨረሻው ደረጃ ላይ የደረሰ መሆኑን ልንገልጽላቸው የግድ ይላል።ሰሞኑን ህወሃት/ኢህአዴግ በአማራ ክልል በባህርዳር ከተማ ባካሄደው ዘጠነኛ ጉባዔ ወያኔና ኦህዴድ መተካካት ሲያደርጉ የደሕዴድና ብአዴን በነበሩት መቀጠላቸውን የሚያበስር ዜና(ወሬ)ስሰማ ከ18 ዓመት በፊት አገር ቤት እያለሁ የማውቀው የዚህ በኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም በአማራ ህዝብ ላይ ጥላቻ የተለከፈ ቡድን ሴራ ትዝ አለኝና ከዚህ በኋላ ልኩን እንደዘለሉ መናገር አለብን ብየ ሃሳቤን በጹሑፍ ማስፈር ጀመርኩ።ብዙዎቻችን የአገር ነቀርሳ የሆኑ የቀድሞ የወያኔ አመራር የነበሩ ከድርጅቱ መገለላቸው ወይም ራሳቸው በፈቃዳቸው መልቀቃቸውን እንደ አንድ እፎይታ ልናየው እንችላለን ይህ ፍጹም የዋህነት ነው።ስብሃት ነጋ የሚረጨውን መርዝ አስቡት ማንን ተማምኖ ነው ስብሃት ይህን ያህል ልሃጩን

የሚተፋብን?ለነገሩ(ጌታዋን ያመነች በግ ላቷን ደጅ ታሳድራለች)እንደሚባለው ስብሃት እነ አዲሱ ለገሰና በረከት፤ሕላዊ የሴፍና ታደሰ ካሳ በሥልጣን እስካሉ ድረስ ስዩም መስፍን አርከበና እነ ብርሃነ ገ/ክርስቶስ ከኋላ ሆነው እንደሚያስተኩሱ መርሳት የለብንም።

በኛ ድክመት ክስ የሚመሰርትበት ጠፍቶ ታምራት ላይኔ የሰራውን ሰርቶ ዛሬ ደግሞ የሃይማኖት መሪ ነኝ ብሎ አገራችን ጥለን መጥተን ተሰደን በምንኖርበት አገር ያሻውን እየወሻከተ ይገኛል።አዲሱ ለገሰ፤ተፈራ ዋልዋ፤ሕላዊ ዮሰፍ፤ታደሰ ካሣ እንዲሁም ድሮ በኢህዴን የድርጅቱ አመራር ላይ የነበሩና ዛሬ ደግሞ ብአዴን ብለው በአማራው ስም በሚቀልዱበት ድርጅት ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ በኃላፊነት ደረጃ ላይ የሚገኙ ኃይሎች አሁን ለምንገኝበት አገራዊ ቀውስ በቀዳሚነት ተጠያቂ ናቸው።ለዚህ መሰረታዊ መነሻየ የደቡብ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት(ድሮ የስምጥ ሸለቆ)፤አህዴድ በኢህዴን ውስጥ የተደራጁ ሲሆን ፊታውራሪዎች ሻብያና ወያኔ ከደርግ ያያዙዋቸውን የደርግ ወታደሮች ለኢህዴን በማስረከብ ወደ መሃል አገር ለወረራ ይረዳ ዘንድ በመሪነት የተጠቀሙበት ሲሆን ዛሬም ለወያኔ የአሽከርነት ተግባራቸውን እየፈፀሙ ይገኛሉ።የዚህ ድርጅት አመራሮች በተለይም በረከት፤አዲሱ፤ታደሰ፤ህላዊ፤ተፈራና ከደሙ ንጹሕ ነኝ የሚለው ታምራት ላይኔ በሐረር፤አርባ ጉጉ ፤ወተርና በደኖ ያን ያህል ሕዝብ ካስጨረሰ በኋላ በጎንደር ከተማ የደቡብ አማራዎችን በመጥራት ከሰሜኑ አማራ ጋር በማገናኘት የተጫወተውን ድራማ እንዲሁም በኢህዴን ውስጥ የአማራ ተወላጅ የሆኑትን በመግደል የታወቁ ናቸው።ለምሳሌ ዘለቀ፤ጌጡ(ኡስማን)፤ንጉሤ ጢሞ፤ሙሉዓለም፤ዓለማየሁ፤ሆሳእና...ወዘተ እንዲሁም የወልቃይትን ጉዳይ አነሳችሁ ተብለው አርማጭሆ ውስጥ አንገረብ ወንዝ ተገድለው ውሃ ውስጥ የተጣሉ የአማራ ልጆች ደም ያፈሰሱ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።በዚህ ነጥብ ላይ ማለት የምለው ወጣት የሆኑ ብአዴን በሚባል ድርጅት ውስጥ የሚገኙ የአማራ ልጆች የሕዝብን ድጋፍና ይሁንታ ለማግኘት ይችሉ ዘንድ በመጀመሪያ ደረጃ መለስ የሰጣችሁን ስም በመቀየር የአማራ ሕዝብ ብሔራዊ ድርጅት በማለት መጠሪያ እንዲኖራችሁ፤በሁለተኛ ደረጃ አማራ ሳይሆኑ በሞግዚትነት ድርጅቱን ለዘር ማጥፋት ተልዕኮ የሚጠቀሙበትን ታደሰ፤አዲሱ፤ሕላዊ፤በረከትና ተፈራን ከአማራ ክልል እንዲወገዱና የሚወክላቸውን ሕዝብ ድርጅት ቢመሩ ወይም ወያኔ ውስጥ እንዲቀላቀሉ ማድረግ መቻል አለባችሁ።ይህ ሳሆን ቢቀር ግን በወያኔ ላይ የሚነድ እሳት እናንተንም ጨምሮ እንዳያቃጥላችሁ አስቡበት እላለሁ።ይህን ስንላችሁ ግን እኛ ጦርነት ናፋቂ ሆነን አይደለም ጦርነትን ግን እናውቀዋለን።ነገር ልኩን ሲያልፍና ሁላችሁም ከሕግ በላይ ሆናችሁ የዘር ማጥፋቱን ከቀጠላችሁበት እሙኑን ጦርነቱን እንጀምረዋለን እኛም በምናውቀው ሜዳ በሚወደን ሕዝብ መህል እንገኛለን ያኔ እውነቱ ይለያል።

እንደሚታወቀው የአገራችን ኢትዮጵያ ታሪክ የሚኀላው የጦርነት ታሪክ ነው።ይህ ደግሞ ኢትዮጵያውያን ጦርነት ናፋቂ በመሆናችን ሳይሆን ምዕራባውያንና ዐረቦች ከየራሳቸው ጥቅም አኳያ ቀይ-ባህርን በመቆጣጠር የአሰብና ምፅዋን ወደቦች መጠቀሚያ በማድረግ።ሰሜናዊውን

የኢትዮጵያን ግዛት በጃቸው ማስገባትና ዐረቦች እስራኤልን ለማጥቃት፤ምዕራባውያን ደግሞ የዐረቡን ዓለም ለመቆጣጠር እንዲችሉ የግድ ይህን አካባቢ እጃቸው ውስጥ ማስገባት ነበረባቸው።ስለዚም ነው በተለያዩ ጊዚያቶች የውጭ ኃይሎች በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት የሚሰነዝሩትና ሲሰነዝሩ የኖሩት። ይሁን እንጅ ሁሉንም እንደ አመጣጣቸውና እንደ አደረሱት ጉዳት መጠን እየተመለከቱ አስተዋይ የሆኑት ቀደምት ወላጆቻችን ተገቢውን ምላሽ በመስጠት የአገራችን ሉዓላዊነት ሕይወታቸውን በመክፈል፤ደማቸውን በማፍሰስና አጥንታቸውን በመከስከስ አሁን ላለው የወላጆቹን ጋሻ ማንሳት ለተሳነው ትውልድ አስረክበውት ነበር።ነገር ግን ይህ ትውልድ የወላጆቹን አደራ ሊረከብና አንድነቱን ጠብቆ የአገሩን ሉዓላዊነት አስከብሮ መቀጠል የማይችል ሆኖ ይገኛል።ይህ ደግሞ የአገሩ ጉዳይ ግዴታና ኃላፊነት ለሚመለከተው ለዚህ ትውልድ መጥፎ ውድቀት እንደሆነ በራሴ በኩል አምናለሁ።ምክንያቱም ግዴታውን ለመወጣት አለመቻሉና ኃላፊነት የሚሰማው ሆኖ ባለመገኘቱ አገራችን አሁን ካለችበት የከፋ የጎሳ ክፍፍል፤አንዱ ጎሳ በሌላኛው መጠራጠር፤መገንጠልን እንደ መፍትሄ መውሰድ፤አንዱን ጎሳ በማነሳሳት በአንዱ ጎሳ ላይ እንዲዘምት ማድረግ ሥር ሲሰድ ከአለበት ላይ እንዲቆምና ለምን? ብሎ ትንሽ ወደ ኋላ ሄዶ ማገናዘብ የማይችል በመሆኑ ነው።ይህን ስል መጀመሪያ ተወቃሽ ማደርገው እኔን ራሴን ሲሆን በዚህ ዙሪያ እንደኔው በማንጎላቸት ላይ ያሉ ኢትዮጵያዊ ወገኖቸ ሁሉ እግዚአብሔር እርስ በእርስ ከመጠላለፍና ከመወነጃጀል አውጥቶ ለአገራችን እንድንታደጋትና ከተወቃሽነትም እንድንተርፍ እመኛለሁ። እዚህ ላይ ግን ሌትና ቀን አገራቸውንና ሕዝባቸውን ለመታደግ በመገናኛ ብዙሃን፤በሰላማዊና በትጥቅ ትግሉ የሚፋለሙትን ረስቸ ሳይሆን ቁጥራቸው አልበዛም፤በአቅም አልጎለበቱም ማለቴ እንጅ።በተለይም ልጆች ያሉን ወይም ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የኛ ተተኪ ትውልዶችና ለአገራችን የምናስብና የምንቆረቆር ሁሉ ምን አይነት ኢትዮጵያንና ምን አይነት የኢትዮጵያ ታሪክ አስረክበን እንደምናልፍ ሰከን ብለን አስበን መልሱን ልንሰጥ የግድ ይለናል።ፈረሱንም ሜዳውንም ለወያኔ ለቀን ምንመለከት ከሆነ ኢትዮጵያ የምትባል አገርና ኢትዮጵያዊ የሚባል ትውልድ ሊኖር እንደማይችል በድፍረት መናገር ይቻላል።ዝርዝሩን እመለስበታለሁ።

አገር በቀል የኢትዮጵያ ጠላቶች ተብለው ከሚታወቁት እኔ እንደተረዳሁት«የዩዲት ጉዲትና የግራኝ መሐመድ»ወረራ ነው።የእነዚህ ሁለት በተለያዩ ወቅቶች የተነሱ አገር በቀል የኢትዮጵያ ጠላቶች ወረራ አገራችን ኢትዮጵያን ክፉኛ የጎዳ እንደነበር ከተለያዩ መጽሐፍት ተመልክቻለሁ።አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ«የግራኝ መሐመድ ወረራ»በሚል ከጻፉት የሁለቱን ወራሪዎች የወረራ አስከፊነት እያወዳደሩም አስፍረውታል።በአገር ሐብት፤በሰው ህይወት፤በአገር ቅርሶችና በኢትዮጵያ ገዳማትና አብያተ ቤተክርስቲያናት ላይ ያደረሱት ጉዳት በጣም አሰቃቂና ዘግናኝ እንደነበር በታሪክ ተዘግቧል።ይህ በአገር አንድነትና በእምነት ነፃነት በአጠቃላይ በፖለቲካዊ ሁኔታ ሲታይ አደገኛ ነበር።ነገር ግን ጥንታዊ ወላጆቻችን የዋዛ አልነበሩምና ሁሉም ተደመሰሱ።

ዛሬ ቴክኖሎጅውና ሳይንሱ ባደገበት በ፳፩ኛው ክፍለ ዘመን ሌላ አገር በቀል ጠላት የወራሪዋን የኢጣሊያ የወረራ መርሕ እንዳለ በመውሰድ(በመኮረጅ) የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ማስደፈር፤አንድነቷን ማፈራረስ፤እምነትን መሸርሸርና ሕዝቡን ሃይማኖት አልባ ማድረግ፤ የአገሪቱን ሀብት መዝረፍ፤ታሪካዊ የሆኑ ቅርሶችን ማጥፋ ወይም መሸጥ፤ማጥፋት፤የአንድ ጎሳ የበላይነት የሰፈነበት ፖለቲካዊ ሥርዓት መመሥረትና የሌላውን ጎሳ ዘር የማጥፋት ርምጃ መውሰድ ፕሮግራሙ ያደረገ ቡድን በ፲፱፷፯ዓ/ም በትግራይ ምድር ራሱን ወያኔ/ህወሃት ብሎ የሚጠራው ተመሰረተ።የህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ መስራቾቹም ሆነ ቡድኑ ከተመሰረተ በኋላ የተቀላቀሉት ዛሬ አገር የሆነችው ኤርትራውያንና የትግራይ ተወላጆች የሚገኙበት ቡድን ሲሆን ይዞት የተነሳው ዓላማ ወይም ፕሮግራም ኢትዮጵያ የምትባል አገርን ማጥፋት፤ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖትን መበረዝ(መንግሥታዊ ሃይማኖት መገንባት)፤አማራና የአማራ ቋንቋን መደምሰስ፤ከአፈር፤ከኤርትራ፤ከወሎና በጌምድር የአማራን ግዛት በመንጠቅ«ታላቋን ትግራይ ትግርኝት ሪፐብሊክ መንግሥት»መመስረት አድረጎ የተነሳ ሲሆን እንደ አብነት ሊወሰዱ የሚችሉ በሽዎች የሚቆጠሩ ማስረጃዎች ቢኖሩም በቀላሉ በደርግ ወቅት ጸረ-ደርግ የነበሩ ድርጅቶችን ኢዲዩና ኢህአፓን የወጋ በተለይም ኢህአፓን በትግራይ መሬት መታገል አይችልም በማለት ብዙ ታጋዮችን የፈጀ ጦርነት ፈጽሟል።ጠቅለል ሲል ወያኔ/ህወሃት ደርግን ሳይሆን ትኩረቱ አድርጎ የተነሳው ጫካ በነበረበት ወቅት ሆነ አሁን የቤተመንግሥት አለቃ ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ በድምሩ ወደ 39 ዓመታት የፈጀው ዓላማ የአማራን ዘር ማጽዳት፤የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን አፍርሶ መንግሥታዊ ሃይማኖት መመስረት እንደሆነ ከተወሰዱት የቡድኑ ርምጃዎች መገንዘብ ይቻላል።

ይህ ዘረኛና ጠባብ ቡድን ራሱን በትግራይ ሕዝብ ጉያ ሥር ቀብሮ የሀሰት ፕሮፓጋንዳውን እያናፋ አማራ የትግራይ ሕዝብ ጠላት ነው ቢልም የትግራይ ህዝብ ምላሽ ሌላ ነበር ዛሬም ቢሆን የትግራይ ህዝብ የአማራ ሕዝብ ጠላቱ እንዳልሆነ ጠንቅቆ ያውቃል።በመሆኑም ከቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር እንደ ድሮው እንደ ጥንቱ አብሮ ይኖራል አብሮም ይቆማል።ህውሃት ሥልጣን ላይ በመውጣቱ የትግራይ ህዝብ ያገኘው አንድም ጥቅም እንደሌለ ራሱ የትግራይ ሕዝብ ይናገረዋል።የቀረው ቢኖር የህወሃትን አፈና ሰብሮ በመውጣት በሌሎች ማለትም በአፋሩ በአኘዋኩ፤በአማራው ላይ ወዘተ..የሚፈጸመውን ግፍ አውግዞ አለመገኘቱ ነው።የህወሃት ገዥዎች ራሳቸውም የትግራይ ህዝብ ብለው የሚቆጥሩት ካድሬውን ፤ደህንነቱን፤ሠራዊቱንና በኢህአዴግ ጃንጥላ ሥር የተሰባሰቡ ነጭ ለባሾችን ድሮ ኢህዴን አሁን አብዴን፤አህዴድ፤ ደህዴድና ወዘተርፈዎችን የሥርዓቱ ጠባቂና ተጠቃሚዎችን ብቻ እንደሆነ ማወቅ ያስፈልጋል።

ከላይ ወደ ኋላ እመለስበታለሁ ወደአልኩት ፍሬ/አርፈተ ነገር ልመለስና አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ እየተፈጸመ ያለው ጥድፊያ የተሞላበት የዘር ማጽዳት ዘመቻ ወያኔ በመላ አገሪቱ የሚያደርገውን ኢኮኖሚያዊና ማቴሪያላዊ ወረራ የቤት ሥራውን ጨርሶ ህዝቡን እርስ በርሱ በማጫረስ

የዋህ ጀሮ ያላቸውንም ነገሩ ሲብስባቸው መገንጠልን እንደ አማራጭ እንዲወስዱና ወያኔም በህልሙ ያለመውን«የታላቋን ትግራይ ትግርኝት ሪፐብሊክ »አዋጅ ለማወጅ ካልሆነ በስተቀር ሥርዓቱ ተንቀርፍፎ በራሱ ጊዜ ወደ መቃብር እየወረደ ባለበት ወቅት አማራን ለይቶ ከየትኛውም የኢትዮጵያ ክልል ማፈናቀል፤ማፈን፤ መግደል፤ ንብረቱን መዝረፍ፤ማሰር የቡድኑ ባህሪ ቢሆንም ይህኛው ለየት ያለ ነው።በ39 ዓመታት ውስጥ አማራው አማራነቱን እንዲጠላ ወይም በአማራነቱ እንዲያፍር(ለምሳሌ በብአዴን ዙሪያ የተሰባሰበውን ነጭ ለባሽ)፤አማራው አንገቱን እንዲደፋ፤ልሳኑ ሲዘጋና አንደበቱ ሲታፈን አሜን ብሎ እንዲቀበል፤በተለያየ ምክንያት አገር ጥሎ እንዲሰደድ ቢደረግም ቋንቋውን ማስተው፤አማራን ጨርሶ ማጥፋት እንደማይቻል የወያኔ ልብ ያውቀዋል ።ይልቁንስ ነገር እንዳይበላሽ በትግስት የተቀመጠውን አማራ መገፋፋቱ የሚያስከትለው አደጋ በቀላሉ የሚበርድ አይመስለኝም።የወሎ ወይም የጎጃምን አርሶ አደር ወይም ነጋዴ እንደ አፄ ቴዎድሮስ-አፄ ምኒልክ-ኃይለሥላሴ-መንግሥቱ በማሰብ የብቀላ ርምጃ መውሰድ ከሆነ ሁሉም በየጊዜያቸው የሚችሉትን ያህል አድረገዋል አፄ ቴወድሮስ የመሳፍንቱን አገዛዝ በማስወገድ አንድ ማዕከላዊ መንግሥት የመሠረቱ ያለ ጊዜው አስቀድመው የሚያስቡ ጀግና ንጉሥ ነበሩ።አፄ ምኒልክም የአፄ ቴወድሮስን ውጥን ከግቡ ያደረሱ የመላ ጥቁር ሕዝብ መመኪያ ነው የነበሩት አፄ ኃይለ ሥላሴም ወደኋላ ነገር ቢበላሽባቸውም የሚችሉትን ያህል በተግባር አስይተዋል እንግዲህ ደርግን ደግሞ በአገር አንድነትና በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ጉዳይ ጠንካራ የነበረ ሲሆን በጨፍጫፊነቱ ግን አሁን ካላችሁት የሚለይ አይደለም።እውነቱን ማወቅ ካስፈለገም ከአፄ ቴወድሮስ በስተቀር ሁሉም አንድ ወጥ የሆነ ዝርያ አልነበራቸውም ዝርያቸው ስብጥር ነበር ይህን የዘር ቆጠራ ለወያኔዎች ልተውላችሁ።በመሠረቱ የኢትዮጵያን ሕዝብ ስብጥራዊ የዘር ሀረግ ለይቶ ለማስተማር የሚከጅሉትን በጥላቻና በመከፋት ያደጉ የወያኔ/ህወሃት መሪዎችና ተከታይ ነጭ ለባሾችን የምጠይቀው ጉዳይ ይኖረኛል ይኸውም ከላይ የጠቀስኳቸውን የአገር መሪዎች ታሪክ አንብበው እንዲረዱ ነው።አዲሱ ለገሠ ኦሮሞ ነኝ ብሎ በድሬ-ቱቢ ተናግሯል እንዲያውም በዚህ ክሊፕ ላይ የአባቱን ትጥቅ ከወንድሙ ጋር በመሆን እንዳስፈታና ያን አባቱ ይከተሉት የነበረውን ስርአትም ታግሎ እንደጣለ ግዳዩን ለጌታው ወያኔ እንዳበረከተ የተናዘዘውን ተመልክቻለሁ፤በረከት ስምኦን እናት አባቱ እርትራዊ እንደሆኑ ይታወቃል ተፈራ ዋልዋ፤ታደሰ ካሳ፤መለስ ጥላሁን፤ተሰማ ገ/ሕይወት፤ሕላዊ ዮሴፍ አማራ ሆነው ነው ወይ የብአዴን መሪዎች ሆነው የተቀመጡት? ሲበዛ ማርም ይመራል። እንዲሉ መረን ያለፈ ጭካኔ የተሞላበት ርምጃ በአስቸኳይ ካልቆመ እኛም ቤት ያለው እሳት በቅርቡ ይነዳል።ከዚያ በፊት ግን ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ሊገነዘበው የሚገባው ነገር ዛሬ በአማራው ላይ እየተወሰደ ያለው እርምጃ ነገ በእያንዳንዱ ቤት ማንኳኳቱ እንደማይቀርና እንደሚደርስ አስቀድሞ ማሰብና ይህን ድርጊት በጋራ ለማስቀም አብሮ መሰለፍ መልካም ነው።

**የተቃዋሚ ድርጅቶችም እውነት በኢትዮጵያ ያለው አስከፊ ሥርዓት ሊወገድ ይገባዋል ብላችሁ እየታገላችሁ ከሆነ በአማራው ላይ በኝዋኩ ላይ ወዘተ..የሚወሰደውን ርምጃ ለመመከት ሕዝቡ በጋራ እንዲነሳሳ ልታደርጉ ይገባል ለፖለቲካ ድርጅቶች ይህ ወቅት ያለረፍት እንድትሰሩ የሚያደርግ ይመስለኛል።በዚህ ወቅት ተሳትፏችሁን ካላሳያችሁ እሳቱ ከተጫረ በኋላ የምታተርፉት ያለ አይመስለኝም።የሕዝቡን ይሁንታና አመኔታ ለማግኘት በጋራና በአንድ ሕበረ-ብሔራዊ ድርጅት ዙሪያ ለአንዲት ኢትዮጵያ ብትታገሉ ኖሮ ወያኔ ይህን ያህል ጊዜ ባልቆየ ነበር አሁንም ጊዜውን ተጠቀሙበት ሁኔታችሁ ከፈረሱ ጋሪውን እንደማስቀደም እየሆነ ይታያልና ከወንበሩ ይልቅ የሕዝቡን ብሶት ማዳመጡ ተገቢ ነው።

**በወያኔ/ኢህአዴግ ዙሪያ ተሰብስባችሁ የሥርዓቱ ጠባቂና ተጠቃሚዎች የሆናችሁ በሙሉ ባሳለፋችሁት የግዛት ዘመናችሁ የአማራውን ዘር ለማጽዳትና የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ለማጥፋት የሞከራችሁት ሙከራ ሁሉ በሕዝብ ተሳትፎ እየከሸፈና ሥርዓቱም እርስ በርሳችሁ የምትባሉበት ደረጃ ላይ አድርሷችሁ ይገኛል።ብትገድሉትም ብታስሩትና ብታስርቡትም፤ብታሰድዱትም፤ሀብት ንብረቱን ብትዘርፉትም፤በአገሩ በኢትዮጵያ የመኖር መብቱን ብትገፉትም ሕዝብ መሃሪ ነውና ዛሬውኑ የሕዝቡን ትግል ብትደግፉ ይመረጣል በተለይ አማራ ሆናችሁ እስከ ዛሬ በሆዳችሁ ስትገዙ የኖራችሁ የአማራውን ሕዝብ ለመሸንገል ለይስሙላ ብአዴን በተባለ ድርጅት ዙሪያ ተሰባስባችሁ ሕዝባችን ስታደሙ የከረማችሁት የተፈጠረውን ችግር እዚህ ላይ እንዲቆም ብታደርጉ ለሁሉም መልካም ነው። ትዕቢቱ ደርግንም አልጠቀመውም።

**ለመከላከያ ሰራዊት፤ደህንነትና ፖሊስ አባላት በሙሉ፡-የህዝቡን አመጽ ለማብረድ የተጠቀማችሁት ርምጃ በእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ወገኖቻችን ላይ፤በተማሪዎች፤በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፤በአኝዋክ ህዝብ፤በአማራ ህዝብ፤በማሰርና በማሰቃየት፤በመግደል፤በማሰደድ ተቀዳሚ ተግባር የምትፈጽሙት እናንተው መሆናችሁን የምትዘነጉት አይመስለኝም። ግን እስከ መቼ?በተለይም ትግርኛ ተናጋሪ ያልሆናችሁት ሥርዓቱ ሳይወድቅ አስቀድሞ የሚያጸዳው እናንተውን እንደሆነ ልነግራችሁ እወዳለሁ።ስለዚህ እጃችሁን ሰብስባችሁ ሕዝቡ የሚሆነውን ብትሆኑ መልካም ነው።ካልሆነ ደግሞ በደርግ ሠራዊት ላይ የደረሰውን እንድታስታውሱ እጋብዛችኋለሁ።

**ለሰፊው የትግራይ ሕዝብ በሙሉ፡- አስቀድሜ የኢትዮጵያ ታሪክ ሲነሳ ቀድሞ ትዝ የሚለኝ የትግራይ ህዝብ ነው።ምክንያቱም ማንኛቸውም አይነት ጥቃቶች በኢትዮጵያ ላይ ሲሰነዘሩ የሚጀምረው በኤርትራና ትግራይ ሲሆን ይህን የረጅም ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ ከሰሩት ኢትዮጵያውያን ቀዳሚው የትግራይ ሕዝብ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።አሁን ግን አገር በቀል የሆኑ የትግራይና የመላው ኢትዮጵያ

ህዝብ ጠላት የሆኑ የህወሃት አመራሮች ድሮ ለ17 ዓመታት ያህል የጫካ ህግ በመከተል በኋላ ቤተመንግሥት ከገቡ በኋላም የኢጣሊያን ፋሽታዊ መመሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ ተግባራዊ በማድረግ 21 ዓመታት አድርገዋል።አማራው ግን አልጠፋም፤ቋንቋውም እየተናገርንበት ነው። ቡድኑ የሚያራምደው ቅጀት የተሞላበት ድርጊት ግቡን ይመታል አይመታም ሌላ ጉዳይ ሆኖ እግረ መንገዱን ግን የትግራይን ሕዝብ እስከ መቸውም የማይጠፋ እሳት እንዳነደደበት መናገር እወዳለሁ።ይኸውም የአፋር፤የኤርትራ፤ የወሎና ጎንደር አማራን በማፈናቀል የተወሰደው መሬት የሚያስከትለው መዘዝና አሁን በአማራ ላይ የተጀመረው የዘር ማጽዳት ዘመቻ ነገ በመላ አገሪቱ የተሰራጨውን የትግራይ ህዝብ እንደሚመለከት ስለሚታየኝ ከአማራው ጋር በመወገን ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ ይህን ጠባብና ዘረኛ ቡድን በጋራ እንድንታገለው ጥሪየን አቀርባለሁ።

በመጨረሻም ትግሬ መሆን ወይም ኦሮሞ ወይም አማራ ወዘተ መሆን ያኮራል እንጅ አንገት የሚያስደፋና የሚያሳፍር አይደለም።እኔ አማራ በመሆኔ እኮራበታለሁ እንጅ አላፍርበትም።አማራ ደግሞ እንዲህ በበረከትና አዲሱ በስብሃትና አባይ ጸሐየ ተዋርዶና ተሰዶ አይቀርም። እያንዳንዱ በሰፈረው ይሰፈራል

ሽፈራው ሽጉጤና መለስ ዜናዊ በመጋቢት/ ሚያዝያ 2012 ኃይለማሪያም ደሳለኝና አህመድ ናስር በመጋቢት/ሚያዚያ አማራ ውጣ ያሉበትና ማፈናቀል የጀመሩት መጋቢትና ሚያዝያ አርሶ አደሩ መሬቱን የሚያለሰልስበትና መሬት ዘር የሚያቀምስበት የዓመት ቀለቡን ለማምረት የመጀመሪያ ወቅት ሲሆን አንድ ግንቦት የነቀለውን ገበሬ...በማሰብ አማራውን በኢኮኖሚ ለማዳከምና የርዳታ ስንዴ ለመለመን እንዲሰለፍ ለማድረግ ነው።

ኢትዮጵያ አንድነቷን ጠብቃ በክብር ለዘልዓለም ትኖራለች!!

አንድነት ኃይል ነው!

ጌታቸው አባጎፍንን